ያመኑት ሲከዳ

ለኢንጅነር ኃይሉ ሻውል

ለሻለቃ ዮሴፍ

ለዶ/ር ታዬና ክህደት አምባ ኩባንያ አባላት
ሃገረ አሜሪካ

ይሆናል በሚል እምነት ነበር ኢንጅነርን ለቅንጅት ሊቀ መንበርነት የመረጥናቸው።
የተሻለም ጠፍቶ አልነበረም ግና ከእድሜ፣ ካለፈ ተዋጽኦ፣ ለመጡበት ድርጅት ካለ አክብሮት፣ ባለፉት አመታት በደረሰባቸው በደል ሳቢያ አሁንም ጠንክረው ያጠነክሩናል ብለን ነበር በሙሉ የጠቅላላ ጉባኤ ድምጽ ያውም በሌሉበት የመረጥናቸው።

አሁን የሚፈሩት በምርጫና ዴሞክራሲያዊ ሂደት የሥልጣን ማጣት ፍርሃት እውነት እንደሚያስቡት የሚያስብ አባልም ሆነ የሥራ አስፈጻሚ ቢኖር ኖሮ በሌሉበት ሊመረጡ አይገባም በሚል ተቀባይነት ባለው ምክንያት ማግለል ይቻል ነበር።እንደሳቸው ፍርሃት የሚያስብ ባለመኖሩ ነው በሌሉበት ሁሉም ለሳቸው በመቆም ሲመረጡ አንዳችም ተቃውሞ ያላሰማው።

የኢንጅነር ፍርሃት ያፈጠጠባቸው አንዳንድ ግብዞች ለጊዜው ያመለጡ መስሏቸው በጋቷቸው የሃሰት ወሬ ላይ ነው።ያ የሃሰት ቅጥፈት ደግሞ በየቀኑ ትናንሽ ውሸቶች እየወለደ የውነትን የሃቅን ቦታ ሙሉ በሙሉ ስለያዘው ለጊዜውም ቢሆን እውነት ተዋጠች።በቅርቡ ግን ጠቅላላ ጉባኤው እውነቱን አጣርቶ በማስረጃ የተደገፈ ሃቅን ሲያጋፈጣቸው ኢንጅነርም በዙርያቸው የተበተቧቸውም የቅጥፈት ቋቶች ጉዳቸው ይዘረገፍና ማፈሪያ ሆነው የቀራሉ፣እስከዚያ ድረስ ግን ጉዳት በቅንጅትም በሕዝብም ህሊና ላይ በመጠኑም ቢሆን ያደርሳሉ።

በውጪ ይህ ሲሆን በሃገር ውስጥ ደግሞ ቅጥር ነፍሰ ገዳዩና ስም አጥፊው ቀንደኛው የቅንጅት ጠላት ሪፖርተር ገዢ አጥቶ የነበረውን ጋዜጣውን በአመራሩ መሃል ያልተፈጠረውን እየፈበረከ፣ ትንሹን ትልቅ በማድረግ እነኢንጅነርም እግዜር ይስጣችሁ በመባል ቃለመጠይቅ እየሰጡ በአለመግባባቱ ላይ ይበልጥ እሳት እያስጫሩ ጋዜጣውን በማሻሻጥ ላይ ናቸው።

ኢንጅነር ኃይሉ በውስጣቸው ተደብቆ የነበረ የሚመስለው ፈላጭ ቆራጭነታቸው አሁን ብቅ እያለ ነው።ለካ ያለ ነገር ሰው ስም አይወጣለትምና፣ በቀድሞው ድርጅታቸው

ውስጥ እያሉ እሳቸውና ምክትሎቻቸው ዘ ጋንግ ኦፍ ፎር ( የአራቱ .. .. .. ቡድን) ይባሉ ነበር በድብቅ።አሁን እውነት እውነት እየሸተተ ነው ያ ስም አወጣጥ።

ኢንጅነር ምን አጥተው ነው እንዲህ አይነት ርካሽ ተንኮልና ጥፋት ውስጥ የገቡት? ሁሉም አሁን እሳቸው  የሚጠሏቸውም የአመራር አባላት አክብረው ጋሼ ብለው ሲመጡ ተነስተው ከበሬታ ሳይነፍጓቸው አይወርዱ አወራረድ ወርደው ከነሻለቃና ከማይታየው ታዬ ጋር የገጠሙት?

ሻለቃ!

ምን ይሁን ምን፣ ማንም ያግዝህ ማንም፣ የትም ተደበቅ የት፣ የሕዝብን አደራ ማስመርመሩ እንደሁ አይቀሬ ነው።ባንተና በዶ/ሩ አመለካከት እቅዳችሁ ኢንጅነርን ይዘን አለን ካጠገብህ ካልነው ለበየቀኑ የሚሆን የወሬ ቡፌ እስካቀረብንለትና ሕዝቡ ባይሆንም ከጎንህ ነው እስካልነው ድረስ ይህንንም እንዳያጣራና እውነቱን እንዳያውቅ ግንኙነቱን እስከዘጋን ድረስ እንዲያውም ማንም ሳያውቅና ሳይሰማ ከዲሲ እስካስወጣነው ድረስ ሚስጥራችን ተደብቆ፣ ቅሌታችን ተሸሽጎ ይከርማል በሚል የሞኝ ዘዴ ለማምለጥ መሞከር የትም አያደርሳችሁም።

ዶ/ር ታዬ

ቅንጅት ሥር የገባህ መስሎህ ሻለቃ ጉያ በመወሸቅ በመምህራን ማህበር የተጠየቅከውን የገንዘብ እዳ  ከሻለቃ ሳይሆን ከቅንጅት አሰባስበህ ከተጠያቂነት ለማምለጥ ጨርሶ አትሞክር። የሚያዋጣ ዘዴ አይደለም።የቅንጅት ንብረት የነካ በእሳት እንደሚጫወት ሞኝ ነውና።

አዩ ኢንጅነር

ዝንጀሮ ዝም ብላ አርፋ ብትቀመጥ ማንም ጉዷን ሳይይ እንዲያው ዝንጀሮ ብሎ ይጠራት ነበር።አንዳንድ ጊዜ ቀበጥ ትልና አለኔ ብልጥ አለኔ ፈጣን አለኔ ተንኮለኛ የለም ብላ ዛፍ መውጣት ስትጀምር ተደብቆ የነበረው የቂጧ ጠባሳ ይታይባትና ትሰደባለች።አሁንም ያጋጠመን ይሄው ነው።አርፎ መቀመጥን የመሰለ ሰላማዊ መንገድ እያለ ወደላይ ያውም ከአቅም በላይ ተወጣና የሕዝብ ንብረት የሆነውን ቅንጅትን፣ የዚህ ንብረቱ ጠባቂ የሆኑትን አመራሮች ነካችሁና መሰደቢያችሁ ታዬ፣ተጋለጠ፣ ታወቀ።ሳያስፈልግ ነገር ፍለጋ አላዋጣምና አሁንም መመለስ ይቻላል።ለሕዝብ ስትሉ፣ ለቅንጅት ስትሉ፣ለራሳችሁም ስትሉ፣ እባካችሁ፣ መባል ያንሳችሁ ይሆን? እንደልማዱ ጫማችሁን እንሳም እንዴ? ያንን ለማስቀረት አልነበር የተቀናጀነው? እናንተ ማፈርያ ሆናችሁ መሳቂያ አታድርጉን።አዬ ጉድ ያመኑት ሲከዳ!!